750/2013

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ አስተዳደር

## መመሪያ ቁጥር 750/2013

መስከረም 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ አስተዳደር

### መመሪያ ቁጥር 750/2013

በከተማ መሬት ይዞታ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 818/2006 አንቀጽ 23፣ ንኡስ አንቀጽ 3 እና አዋጁን ተከትሎ በወጡ የከተማ ካዳስተር ቅየሳ ደንብ ቁጥር 323/2006 አንቀጽ 22 በተደነገገው መሰረት ለካዳስተር ሥራ የሚውሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች የደህንነት ጥበቃ በማድረግ በዘላቂነት ማገልገል እንዲችሉ እና በተለያዩ አደጋዎች የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ሲበላሹ በምትኩ ሌላ መተካት እንዲቻል እና ጉዳት ያደረሰው አካል ላይ የሚገባውን አስተዳደራዊ እርምጃ ለመወሰን በማስፈለጉ፤

የከተማ ካዳስተር ቅየሳ ሥራ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን እና በስታንዳርዱ መሰረት እንዲፈፀም የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችም ሆኑ የመሬት ይዞታ ወሰን ምልክት በሚመለከታቸው አካላት እና በባለይዞታው ጥበቃ እንዲደረግ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 750/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ስታንዳርዱ"** ማለት የከተማ ህጋዊ ካዳስተር ስታንደርድ ቁጥር 03/2015 ነው፡፡
2) **"ቅየሣ"** ማለት በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ የሚገኙትን ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ አካላት አንጻራዊ አቅጣጫ፣ ርቀትና ከፍታን በመለካት የቦታውን መገኛ፣ መጠንና ቅርጽ ለማሳየት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡
3) **"ቀያሽ"** ማለት ማንኛውም የከተማ ካዳስተር ቅየሳ የሚሰራ የካዳስተር ቀያሽ ወይም ልዩ ፈቃድ የተሰጠው ቀያሽ ነው፡፡
4) **"የቅየሣ መቆጣጠሪያ ነጥብ"** ማለት በምድር ገጽ ላይ የሚገኝን አንድ ቦታ በካርታ እና በሌሎች የምድር መረጃዎች ላይ ለማመልከት የሚረዳ ወይም የቅየሳ ሥራዎች በሚሰራበት ጊዜ ለልኬት መነሻነት የሚያገለግል የታወቀ መነሻ ነጥብ ነው ፡፡
5) **"የወሰን ምልክት"** ማለት የመሬት ይዞታ ወሰንን ለመለየት በመሬት ላይ የሚታይ የችካል፣ የአጥር ማዕዘን ወይም ሚስማር የተተከለበት ወይም የማይጠፋ ቀለም የተቀባ ምልክት ነው፡፡
6) **"ሞኑመንት"** ማለት የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ቁስ ወይም በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ቁስ ላይ የተመላከተ የቅየሳ ፕላን ምልክት ሲሆን ስልጣን በተሰጠው ተቋም በቅየሳ ዘዴ የይዞታ ወሰን ወይም ነጥብን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመትከል ወይም በድጋሚ ለመትከል የተቀመጠ ድንጋይ ነው፡፡
7) **"የቅየሳ ጥራት ደረጃ"** ማለት የቅየሳ ስራ ሲሰራ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችለውን ስህተት ለመቀበል የሚያስችል ተቀባይነት ያለው የስህተት ደረጃ ነው፡፡
8) **"የደህንነት መጠበቂያ አጥር"** ማለት በከተሞች የተሰፋፉትን የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ከተለያዩ አደጋዎች እንዲከላከል በአካባቢው የሚገኙ ግብዓቶችን በመጠቀም የሚታጠር አጥር ነው፡፡
9) **"የሚመለከተው ተቋም"** ማለት የካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ለማስተዳደር በክልል ወይም በከተማ ደረጃ ሥልጣን የተሰጠው አካል ወይም ተቋም ነው፡፡
10) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
11) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃ ወይም ከዛ በታች ያሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በተስፋፉባቸው በአገሪቱ ዉስጥ በሚገኙ ሁሉም ከተሞች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4. **የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች አስተዳደር ዓላማ**

1) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ደህንነት የሚጠበቅበት ሥርዓት በመዘርጋት ማንኛውም የቅየሳ ሥራ የመነሻ ነጥቦቹን በመጠቀም ጥራት ያለው የቅየሳ ስራ እንዲሰራ ለማድረግ፣
2) በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ላይ ለሚደርስ ጉዳት እና ብልሽት የሚመለከተው ተቋም ተከታትሎ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ በማድረግ በድጋሚ ለመትከል የሚደረገውን ወጪ ለመቀነስ፤
3) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች የመረጃ አያያዝ ስርዓት ወጥና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ለመደንገግ ነው፡፡

<u>ክፍል ሁለት:- ስለ ቅየሣ መቆጣጠሪያ ነጥቦች</u>

5. **በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ዓይነት**

1) በከተሞች እና በአጎራባች ገጠር አካባቢ በየአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ተስፋፍተው የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጥበቃ፤
2) በከተሞች ለካዳስተር ቅየሳ ስራ ሲባል የሚስፋፉ የሶስተኛ ደረጃ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች፤
3) በከተሞች በይዞታ ማረጋገጥ ሥራ የቁራሽ መሬት ወሰን ለመለየት የሚተከሉ የወሰን ምልክቶች ናቸው፡፡

6. **የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጥበቃ አስፈላጊነት**

1) በከተሞች የሚደረጉ የካዳስተር ቅየሳ ስራዎች ጥራትን በማስጠበቅ የቅየሳ መረጃዎች ተናባቢ እንዲሆኑ፤
2) ከተሞች የካዳስተር ቅየሳ ስራ በሚሰራበት ጊዜ የቁራሽ መሬትን ወሰን ከአጎራባቾቹ ለመለየት ለሚደረግ ቅየሳ እና የይዞታ ወሰን ለመለየት መነሻ ሆኖ ስለሚያገለግሉ፤
3) በተለያዩ ምክንያቶች የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ሲፀዳሽ ወይም ይዘቱን ሲለቅ በቅርበት ከሚገኝ ነጥብ በመነሳት እንደገና ለመትከል ስለሚያስችል፤

7. **የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ለይዞታ ወሰን ምልክትነት ስለመጠቀም**

1) በቁራሽ መሬት ቅየሳ ወቅት የይዞታ ወሰን ምልክት ለማስቀመጥ አመቺ በማይሆኑባቸው ስፍራዎች እና በቅርበት የሚገኘው የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ የተበላሸ መሆኑ ሲረጋጋጥ ለይዞታ ወሰንነት መጠቀም ይቻላል፡፡
2) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቡ ለይዞታ ወሰንነት ከዋለ ይህንኑ ለማመላከት የተለየ ምልክት (ቀለም ወይም ጭረት) በመቆጣጠሪያ ነጥቡ ላይ በማድረግ መለየት ያስፈልጋል፡፡ ይህ በሚከሰትበት ጊዜ:-
   ሀ) ልዩነቱን ባካተተ መልኩ ቀያሹ በቅየሳ ንድፍ በግልጽ ያስፍራል፤
   ለ) በመረጃ አደራጀጀት ጊዜም ይኸው አገልግሎት ታሳቢ መደረግ አለበት፤

8. **በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ አናት ላይ በሚለጠፍ ፕሌት ወይም ቀብ ላይ ስለሚገለፁ መረጃዎች**

1) በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ፕሌት ላይ በቋናነት የሚሰፍሩ መረጃዎች፣ የመቆጣጠሪያ ነጥቡ መለያ ኮድ፣ መቆጣጠሪያ ነጥቡ የተተከለበት ዓ.ም፣ የከተማው ስም በምህፃረ ቃል፣ የተከለው ተቋም ስም በምህጻረ ቃል እና ነጥቡ የተተከለበት ሰፈር ስም ከግራ ወደ ቀኝ መፃፍ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፁ መረጃዎች በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ፕሌት ላይ ሲጻፍ ጽሁፉ የሚነበብ እና ፕሌቱ በቀላሉ ተገንጥሎ በማይነሳበት አግባብ መሆን አለበት፡፡

9. የተበላሸ ወይም የተደመሰሰ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ስለመተካት

1) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ በተበላሸበት ቦታ ሌላ እንዲተካ ችግሩን የለየው ቀያሽ ለቅየሳ ሹሙ በማሳወቅ ፈቃድ ሲያገኝ የመተካት ሥራው መሰራት አለበት፡፡

2) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ሞኑመንት በሚበላሽበት ጊዜ ሌላ መተካት ያለበት ሲሆን የበፊቱ መረጃ እንዳይቀየር እና እንዳይጣባ ጥንቃቄ በማድረግ እና በተጨማሪም ሌሎች መረጃዎች ካሉ መጻፍ አለበት፡፡

3) የቅየሳ ነጥብ ምልክቱን መናጋት የለየው ቀያሽ ሞኑመንቱ ከመነሳቱ በፊት ያለውን የከፍታ እና የአግድመት ልኬት በማድረግ ከሌሎች ነጥታዎች ጋር ያለውን ትስስር በማጤን የጥራት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከ28 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲተከል ማድረግ አለበት፤

4) ሞኑመንቱ በተነሳበት ቦታ ሌላ መተካት የማይቻል ሆኖ ከተገኘ፤ ምክንያቱን በማብራራት ይህንን ተግባር የሚያስፈጽመው ቀያሽ ለቅየሳ ሹም በ28 ቀናት ውስጥ ማሳወቅ አለበት፡፡

5) የቅየሳ ሹሙ የተተኩ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ደረጃውን ጠብቆ መተከላቸውን እና ኮድ ተሰጥቷቸው መመዝገባቸውን ሥራው በተፈጸመ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ማረጋገጥ አለበት፡፡

6) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ በድጋሚ ሲተከል የቦታ ጥናት በማድረግ እና በጥናቱ ወቅት ህብረተሰቡን በማሳተፍ ለጎርፍ እና ለሌሎች ፍሳሽ ተጋላጭ በሚሆኑ ቦታዎች፣ በቀላሉ የመሬት መንሸራተት ባለበት፣ ደረቅ ቆሻሻ ከሚጠራቀምበት አካባቢ ላይ እንዳይተከል ውጤቱን መሰረት አድርጎ መሆን አለበት፡፡

7) ሞኑመንቶች በድጋሚ ሲተከሉ የሚተከሉበት ቁሶች ጥራት ያላቸው እና በስታንዳርዱ መሰረት መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

10. ለቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ስለሚገነባ የደህንነት መጠበቂያ አጥር

1) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በቀላሉ ለአደጋ እንዳይጋለጡ ዙሪያቸዉን ለቅየሳ መሳሪያ ማቆሚያ፣ ለባለሙያ መዉጫና መግቢያ እና በአየር ላይ ቅየሳ ዘዴ በማያስቸግር መልኩ በብረት ወይም በድንጋይ ወይም በእንጨት ወይም በማጣመር መታጠር አለበት፡፡

2) የአጥር አዘገጃጀቱ በስታንደርዱ አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.5 መሰረት መሆን አለበት፡፡

3) ለአጥር ግንባታ የሚዉሉ ግብዓቶች የጥራት ደረጃቸው በሚመለከተው ተቋም መረጋገጥ አለበት፡፡

4) ለአጥር ግንባታ የሚዉሉ ግብዓቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአካባቢው የሚገኙ እና በቀላሉ የማይበላሹ መሆን አለባቸው፡፡

5) አጥሩ ለከተማ ካዳስተር ቅየሳ ስራ የሚያገለግል መሆኑ ለማንኛውም ሰው ግልጽ እና የማያሻማ መሆን አለበት፡፡

6) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ መከላከያ አጥር ከሌሎች ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጋር ትይዩነትን በማይጋርድ መልኩ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

**11. የከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ጽ/ቤት ወይም የሚመለከተው ተቋም  በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ አስተዳደር ላይ ስለሚኖረው ኃላፊነት**

1) በከተሞች በሁለተኛ ደረጃ እና በሶስተኛ ደረጃ የተመሰረቱ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ደህንነትን ለመከታተል የስራ እቅድ በማውጣት በየሩብ ዓመቱ ክትትል በማድረግ ያሉበትን ደረጃ ለክልል ተቋም ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡
2) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ደህንነት ሊከታተሉ የሚችሉ አካላትን በከተማው አነስተኛ የአስተዳደር እርከን በመሰየም የነጥቦቹን ደህንነት ጥበቃ በተመለከተ በየወሩ እና ጉዳት ሲደርስባቸው ከ3 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሪፖርት የሚያደርግበትን ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡
3) በከተሞች ያሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ምልክቶች በስታንዳርዱ መሰረት መሆናቸውን በማረጋገጥ ይረከባል፡፡
4) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጉዳት ሲደርስባቸው በአካባቢው ያለው ህብረተሰብ ጥቆማ የሚሰጥባቸው መንገዶችን በማመቻቸት፣ ከህብረተሰቡ ጠባቂ በመወከል እና ሌሎች እንደ ከተማው ነባራዊ ሁኔታ ሊተገበሩ የሚችሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
5) የካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች መረጃ የመረከብ እና በአግባቡ የማደራጀት፣ ወቅታዊ የማድረግ፣ የመጠበቅ እና ለተጠቃሚ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡
6) በመንገድ ጥገና ወቅት በመንገድ ዳር የተተከሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች እንዳይበላሹ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡
7) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን እና የይዞታ ወሰን ምልክቶችን ያበላሸ ወይም የደመሰሰ አካል በህግ ተጠያቂ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡
8) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ከተመሰረተ በኋላ ለደህንነት ጥበቃ እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ የደህንነት አደጋዎችን ለመከላከል የሚያስፈልግ በጀት መያዝ አለበት፡፡
9) የከተማው መሬት ምዝገባ ተቋም የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ማንበብ እና ማስፋፋት የሚችሉ ክህሎት እና እውቀት ያላቸውን የቅየሳ ባለሙያዎችን ማሰማራት አለበት፡፡

**12. የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብን በሚመለከት ግንዛቤ ስለመፍጠር**

1) የከተማ አስተዳደሩ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ጽ/ቤት ወይም የሚመለከተው ተቋም የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ደህንነት አጠባበቅ ላይ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ግንዛቤ የማስጨበጥ ኃላፊነት አለበት፡፡
2) የከተማ አስተዳደሩ የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ጽ/ቤት ወይም የሚመለከተው ተቋም ስለቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በአመታዊ እቅድ ውስጥ አካቶ መፈፀም አለበት፡፡
3) ለቅየሳ መነሻ ነጥብ ማስቀመጫነት የሚዉሉ ቦታዎች ህንጻ፣ የግቢ አጥሮች እና ሌሎችም ላይ ሲሆን ባለይዞታዎቹ ስለ ምልክቶቹ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡

13. **የካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች የደህንነት ጥበቃ ኃላፊነት ስለመስጠት**

1) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ምልክት በአረንጓዴ ቦታዎች ላይ ተተክሎ ከሆነ የከተማዉ ጽዳትና ዉበትን የሚከታተል የስራ ክፍል ኃላፊነቱን እንዲወስድ መደረግ አለበት፡፡
2) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ምልክት ከመንግስት ወይም ከግል ተቋማት አጠገብ ተተክሎ ከሆነ በአጠገቡ ያለው ተቋም ኃላፊነት እንዲወስድ መደረግ አለበት፡፡
3) የመቆጣጠሪያ ነጥቦች ምልክት በግል ይዞታ ላይ የተተከለ ከሆነ ለባለይዞታዉ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲወስድ መደረግ አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 3 የተመለከተው እንዳለ ሆኖ ባለይዞታው የነጥቡን ደህንነት እስከጠበቀ ድረስ የመከላከያ አጥር ማስቀመጥ አያስፈልግም፡፡
5) የመቆጣጠሪያ ነጥቦች ምልክት በንግድ ቦታዎች አጠገብ ተተክሎ እንደሆነ ቅርብ ለሆነዉ የንግድ ቦታ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲወስድ መደረግ አለበት፡፡
6) የመቆጣጠሪያ ነጥቦች ምልክት በመንገድ ዳር ተተክሎ ከሆነ ለዕይታ ቅርብ ለሆነዉ የመንግስት ተቋም ወይም የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ኃላፊነት እንዲወስድ መደረግ አለበት፡፡
7) የመቆጣጠሪያ ነጥቦች ምልክት ያረፈበት ቦታ የሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ይዞታዎች ኩታ ገጠም ላይ ከሆነ ለአጎራባቾች ኃላፊነትና ተጠያቂነት መስጠት አለበት፡፡
8) ይህ የካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች የደህንነት ጥበቃ ኃላፊነት አደጋው በደረሰ 72 ሰዓት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅና ተገቢውን መረጃ መስጠት አለበት፡፡

14. **የካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ደህንነት ለሚጠብቁ አካላት ስለሚደረገው ማበረታቻ**

1) በግለሰብ ይዞታ ላይ የሚያርፉ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ደህንነት ለሚጠብቁ ባለይዞታዎች እንደ ከተማው አቅም እና ተጨባጭ ሁኔታ ማበረታቻ ሊደረግ ይችላል፡፡
2) የተበላሸ ወይም የተጎዳ የቅየሳ መቆጣጠሪያን አይቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ለሚያደርግ ሰው እንደ ከተማው አቅም እና ተጨባጭ ሁኔታ ማበረታቻ ሊደረግ ይችላል፡፡

15. **ስለ ካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች መረጃ አደረጃጀትና አያያዝ**

1) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በከተማው አነስተኛ የአስተዳደር እርከን ደረጃ ብዛት፣ ያሉበት ሁኔታ፣ መገኛቸው፣ የቦታው ልዩ መጠሪያ፣ ፎቶ እና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች በዲጂታል እና በወረቀት ኮፒ ተደራጅቶ መቀመጥ አለበት፡፡
2) በከተማው የሚገኙ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች በከተማው ወቅታዊ መሰረታዊ የካዳስተር ካርታ ወይም ኦርቶ ፎቶ ላይ መመላከት አለባቸው፡፡
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት መረጃዎች በተጠቃሚዎች በሚፈለግ ጊዜ ለአገልግሎት የሚውል መሆን አለበት፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱት መረጃዎች በሚመለከተው አካል የሚመጡ ለውጦችን ተከትሎ ወቅታዊ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**16. የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ላይ ጉዳት ሲደርስ ሪፖርት ስለማድረግ**

1) የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ላይ በተለያየ ምክንያት ጉዳት ሲደርስ ለከተማው ለሚመለከተው ተቋም ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡
2) የነጥቡን ብልሽት አስመልክቶ ጥቆማው እንደደረሰ ባለሙያው በክትትል ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ የነጥቡን ልዩ መለያ ኮድ፣ የቦታው ስም፣ ከተማ፣ የተቋሙ ስም፣ የቀያሹ ስም፣ ፊርማ፣ ቀን እና ሌሎች መረጃዎችንም አካቶ ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

<u>**ክፍል ሶስት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**</u>

**17. ስለ ተጠያቂነት ዓይነቶች**

1) ማንኛዉም አካል በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥበቃ ሊያደርግ ይገባል፡፡
2) በማንኛዉም ደረጃ በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ላይ ጉዳት ሲደርስ ለሚመለከተዉ ተቋም በ72 ሰዓት ውስጥ አለማሳወቅ ተጠያቂ ያደርጋል፤
3) በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን የነቀለ ወይም ያንቀሳቀሰ ማንኛዉም አካል መልሶ የመትከል ወይም መልሶ ለማቋቋም የሚያስወጣዉን ወጪ የሚመጥን ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለበት፤
4) የመንግስት ተቋምም ሆነ የግል ወይም የልማት ድርጅት በቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብ ላይ ጉዳት ቢያደርስ መቆጣጠሪያ ነጥቡ ጥራቱን በጠበቀ መልኩ መልሶ መተካት የሚያስችል ክፍያ መሸፈን አለበት፤
5) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቡን ያበላሸው አካል ካልታወቀ በከተማ ደረጃ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥብን ለማስተዳደር ኃላፊነት ያለው ተቋም መተካት አለበት፤
6) በካዳስተር ቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቡ ላይ መቆም፣ መቀመጥ፣ እቃ ማስቀምጥ፣ በዙሪያዉ ደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀም፣ ዙሪያዉን መቆፈር፣ የሚመለከተዉ ተቋም ሳይፈቅድ መንቀልና ማንቀሳቀስ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

**18. ስለቅጣት አወሳሰን**

የቅየሳ መቆጣጠሪያ መነሻ ነጥቦች እና የወሰን ምልክት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ያጠፋ፣ አጥሩን ያፈረሰ፣ ምልክቱን የቀየረ፣ ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያዛወረ የከተማ ካዳስተር ቅየሳ ደንብ ቁጥር 323/2006 አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይቀጣል፡፡

**19. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**20. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ በማስፈጸም ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

21. መመሪያ ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዲሻሻል ባስፈለገ ጊዜ የፌዴራል የከተማ መሬት እና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የማሻሻያ ሃሳብ አቅርቦ በከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒ ካቢኔ ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፡፡

22. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 01 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጃንጥራር አባይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር